ስሉው ፋድ*

ስሉው ፋድ ሩውንዲሽን
ስጠንዞን ህይወት

የንቦች በረከት

ስሎው ፉድ

ስሎው ፉድ®

በካርሎ ፔትሪኒ ኢ.ኤ.አ በ1986 ዓ.ም የተጀመረው «ስሎው ፉድ» አለም አቀፍ ማህበር የሆነው በ1989 ነው። አሁን የ86ቪ አባላት ባለፀጋ የሆነው ስሎው ፉድ፣ በተከታታይ በጣሊያን፣ በጀርመን፣ በስዊዘርላንድ፣ በአሜሪካ፣ በፈረንሳይ፣ በቻን እና በእንግሊዝ ቢሮዎችን መክፈት በ130 አገራት ደጋፊዎችን ለማግኘት በቅቷል።

ስሎው ፉድ፣ ከምግብ ለምናገኘው እርካታና ደስታ ከፍተኛ ዋጋ መስጠት እንደሚያስፈልግ ያምናል። በብዙ የምግብ አይነቶችና ጣእሞች መደሰትን መማር ይገባናል፣ ምግብ ለሚያመርቱ የተለያዩ ህዝቦችና አካባቢዎች እውቅና መስጠትም ይኖርብናል። የተለያየ ምግብ የምናገኝበት የመትት ፍርርቆሽ ዜማና ተስማሚነትን ማክበር አለብን። ካርሎ ፔትሪኒ እና ሌሎች የስሎው ፉድ አባላት የፈጠሩት የምግብ ጥንቅር በተጨማሪ አዲስ ሃሳብን የሚሰነዝር ነው፣ ሁላችንም በምግብ የመደሰት መብት አለን፣ ይኼ የደስታና የእርካታ ፍሊጋ ግን አዲስ የሃላፊነት ስሜትን የሚጨምር ነው።

ስሎው ፉድ፣ ይህንን አዲስ አትጣጫ ኢኮጋስትሮኖሚ ብሎ ሰይሞታል። ለኢኮጋስትሮኖሚ ባህል አክብሮትና ትኩረት በመስጠት በአለማችን ዙሪያ ለምግብና ለእርሻ ብዝሃ - ህይውት ጥበቃ ለሚታገሉት ድጋፍ ከመስጠት ጋር የሚያጣምር ዝንባሌ (አመለካከት) ነው።

ምግብን የማጣጣም ትምህርት ላይ ስሎው ፉድ አፅንኦት የሚያደርገው፣ የምግብ ጥራት ጉድለትንና የምግብ ብረዛን የምንታወግበት ተመራጩ መከላከያ በመሆኑ ነው።

የጥድፊያ (የሩጫ) ምግብ በእለት ተእለት አመጋገባችን ላይ የጀመረውን ወረራ የምንዋጋበት ዋነኛ መንገድ ነው።

የየአካባቢው ምግቦችን፣ ባህላዊ ምርቶችን፣ አትክልቶችንና እንስሳትን አሁን ከተጋረጠባቸው የመጥፋት አደጋ ለመጠበቅ ይረዳል።

ጤናማና፣ ፉታ የለሽነትን የሚቀንስ አዲስ የእርሻ አሰራርን ይደግፍ ሲሆን፣ በየአካባቢው ማህበረሰብ እውቀትና ክህሎት ላይ የተመሰረተ ነው። ይህ አዲስ የእርሻ አሰራር፣ በጣም ድሃ ለሆኑ የአለማችን አካባቢዎች የልማት ተስፋን የሚሰጥ ብቸኛ መንገድ ነው።

በእነዚህ ምክንያቶች፣ ስሎው ፉድ ምግቦችን፣ የምግብ ግብአቶችን እንዲሁም ባህላዊ የምርትና የአዘገጃጀት ዘዴዎችን ከጥፋት ለመጠበቅ ቆርጦ ይሰራል። ስሎው ፉድ የእርሻና የወፍ ዘራሽ ብዙሀን ህይወትን ለመጠበቅ እንዲሁም በታሪካዊ፣ ጥበባዊና ማህበራዊ ፋይዳቸው ምክንያት የባህላዊ ቅርስ አካል የሆኑ ተስማሚ የደስታ ቦታዎችን ለመንከባከብ ያልማል።

ስሎው ፉድ ለእነዚህ ጉዳዮች የራሱ ልዩ አካሄድ አለው። የአመጋገብ እርካታንና ደስታን ለመደገፍ እንዲሁም የተረጋጋና አስተዋይነት የታከለበት የህይወት ጉዞን ለማለም የተመሰረተው የስሎው ፉድ ፍልስፍና፣ ትኩረቱን ከምግብ ፀጋዎች በተጨማሪ የህይወት ጣእምንና ማንነትን ጭምር ወደማስብ አስፍቷል።

ፍልስፍናው በእርስበርስ የማንኙነት መረብ ውስጥ በሚካሄደው መስተጋብር፣ ለእያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍል ታሪክና ባህል አውትና የመስጠት አላማ አለው። አንድ የፍራፍሬ አይነትን ወይም አንድ ባህላዊ ምግብን ስናስብ፣ ከታሪክ፣ ከቁሳዊ ባህልና ከአካባቢው ስነ-ምህዳር ጋር ያለውን ማንኙነት በቸልታ ማለፍ እንችልም።

ስሎው ፉድ ግብርናና የእንስሳት እርባታ፣ ከአካባቢው ስነምህዳር ጋር የአክብሮትና የልውውጥ ማንኙነት ሚዛን እንዲጠብቅ የማድረግ አስፈላጊነትንም በአጽንኦት ያምናል።

በዚህም ምክንያት ነው ስሎው ፉድ፣ የኢኮጋስትሮኖሚ እንቅስቃሴ የሚል ብያኔ የተሰጠው።

ከ86ቪ የሚበልጡ አባላት ያሉት የስሎው ፉድ እውታር፣ በየአካባቢ ቡድኖች ተደራጅቷል። በጣሊያን ኮንዶቴ፣ እነዚህ ቡድኖች ኮንዶቴ እነዚህ ቡድኖች ኮንዴቴ በመባል ሲታወቁ እንዲሁም በሌሎች የአለማችን ክፍሉች ኮንበቪቭያ ብለው ይጠራሉ። ቡድኖቹ በመሪዎቻቸው አስተባባሪነት፣ ትምህርት ፕሮግራሞችን እንዲሁም፣ የቅምሻና የእራት መስተንግዶዎችን ያዘጋጃሉ፣ በየአካባቢያቸው ቅስቀሳ ያካሂዳሉ፣ በስሎው ፉድ ማህበር በሚከናወኑ አለምአቀፍ ዝግጅቶችም ይካፈላሉ። በጣሊያን የሚገኙ 410 ኮንዶቴዎችን ጨምሮ ከ1ቪ በላይ የሚሆኑ የስሎው ፉድ ኮንቪቪያዎች በ130 አገራት እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ።

የመረጃ ቢሮ፣ ስሎው ፉድ፣ Via della Mendicita Istruita 14-12042Bra(CN) -Italy
ስልክ፣ +390172419615/45/53/66-, press@slowfood.it-www.slowfood.com

ስሎው ፉድ ፋውንዴሽን ለብዝሃን ህይወት

የስሎው ፉድ የብዝሃ - ህይወት ፋውንዴሽን፣ በአለም ዙሪያ የምግብ ብዝሃ - ህይወትን እና የምግብ ባህሎችን ለመጠበቅ ገንዘብ እያሰባሰበ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል። አካባቢን፣ የህዝቦች ባህላዊ ማንነትንና የእንስሳት ደህንነትን የሚያከብር ዘላቂ የእርሻ አሰራሮችን ፋውንዴሽኑ በተለያዩ በርካታ ፕሮጀክቶች አማካኝነት ያበረታታል።
ስሎው ፉድ የብዝሃ ህይወት ፋውንዴሽን የተቋቋመው እ.ኤ.አ በ2003 ከተስካኒ ክልል አስተዳደር ጋር በአጋርነት በፍሎረንስ ከተማ ነው። ፋውንዴሽኑ ገንዘብ የሚያሰባሰበው ከስሎው ፉድ ንቅናቄ፣ ከተለያዩ ተቋማት፣ ከግል ኩባንያዎች፣ ከሌሎች ፋውንዴሽኖችና ብዝሃ ህይወትን ለሚጠብቁ ፕሮጀክቶች ድጋፍ ከሚሰጡ ማንኛውም ወገን ነው።

ስሎው ፉድ ፋውንዴሽን፣ የብዝሃ ህይወት እሳቤ በሰብአዊ፣ በዜግነታዊና በዲሞክራሲያዊ እድገት ድርሻ ስላለው እሳቤውን ይደግፋል፣ ያሰራጫል። በማንኛውም አገር የምግብ ትውፊቶችን እንዲሁም የአካባቢ፣ የግብርናና የእደጥበብ ቅርሶችን ለመጠበቅ ይሰራል። በአለም ዙሪያ በርካታ ፕሮጀክቶችን የሚደግፍ ቢሆንም፣ ዋነኛውና ሁነኛው ትኩረቱ በታዳጊ አገሮች ላይ ነው።

ስሎው ፉድ በእነዚህ አገራት ብዝሃ ህይወትን የመጠበቅ ትርጉም የሰዎችን የህይወት ጣእም ማሻሻል ብቻ ሳይሆን፣ የህይወት ዋስትና መስጠትም ነው ብሎ ያምናል።

- ከኢኮኖሚና ከመዋቅራዊ እይታ፣ የፋውንዴሽኑ ቀዳሚ ፕሮጀክት፣ የፕሬዚዲያ ፕሮጀክት ነው። ዛሬ በ42 አገራት ጥቃቅን አምራቾችን ለመደገፍና የእደጥበብ ውጤቶችን ጥራት ለመጠበቅ የተቋቋሙ ከ300 በላይ ፕሬዚዲያዎች አሉ። ለስሎው ፉድ አውታር አባላት ፣ ለመሪዎች፣ ለተመራማሪዎች፣ ለፀሐፊዎች፣ ለሼፎች (ለምግብ ጠበብቶች) እና ለአምራቾች ምስጋና ይግባቸውና፣ ፋውንዴሽኑ የአመራረት ቴክኒኮች እንዲሻሻሉ፣ አዳዲስ ምርቶች ወይም አዳዲስ የአጠቃቀም ዘዴዎች እንዲፈጠሩ እንዲሁም ምርቶች አካባቢያዊና ዓለማቀፋዊ ገበያ እንዲያገኙ ለማገዝ ችሏል።

- የፋውንዴሽኑ ሁለተኛውና ጠቃሚ ፕሮጀክት «ዘ አርክ ኦፍ ቴስት» ሲሆን፣ የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው ግሩም የምግብ ምርቶችን የሚመዘግብ ፕሮጀክት ነው። በ17 ብሔራዊ ኮሚሽኖቻችን ውስጥ በተካተቱ ባለሙያዎች በተደረገው ጥናት፣ በ50 አገራት የሚገኙ ከ700 በላይ የምግብ ምርቶችን ለፕሮጀክቱ ተመርጠዋል።

- መርካቲ ዲላ ቴራ በተሰኘው ፕሮጀክት፣ ፋውንዴሽኑ በአለም የግብርና ገበያዎች መካከል የግንኙነቶች ግንባታ፣ ስርፀትና ትግበራን ይደግፋል። በአምራቾችና በአከፋፋዮች መካከል የአገናኞችን ሰንሰለት በማሳጠርና ቁጥሩን በመቀነስም ምግብ ከመስክ ወደ ማዕድ የሚጓዝበትን ርዝመት እንዲያጥር ያደርጋል።

- ስሎው ፉድ ፋውንዴሽን፣ በቴራ ማድሬ ፕሮጀክት በተለያዩ የምግብ ማህበረሰብ አባላት መካከል የመረጃና የአውቀት ልውውጥን ያበረታታል። በየሁለት አመቱ በቱሪን በሚካሄደው የቴራ ማድሬ ዝግጅት፣ ከ130 አገራት የሚመጡ 5000 አምራቾች ይሳተፉበታል።

የመረጃ ቢሮ፣ ስሎው ፉድ፣ Via della Mendicita Istruita 14-12042Bra(CN) -Italy
ስልክ፣ + 390172419615/45/53/66-, press@slowfood.it-www.slowfood.com

የንቦች በረከት

ማውጫ

መግቢያ	5
በቀፎ ውስጥ ያለው የህይወት ኡደትና አደረጃጀት	8
የንቦች መዋቅረ - አካል	12
የንብ አርቢው መሳሪያዎች	14
የቀፎዎች አያያዝ	18
ባህላዊና ዘመናዊ ቀፎዎች	21
ማርን የመቁረጥና የማጣራት ዘዴ	24
ንግስት ንብ ማሳደግ	26
ማጠቃለያ	30

መግቢያ

የንብ እርባታ ከሌላ የእንስሳት እርባታ ጋር ሲነፃፀር በርካታ ጥቅሞች አሉት። ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።
- ንቦችን እንደሌሎች እንስሳት መመገብ አያስፈልግም፣ ዓመቱን ሙሉ ራሳቸው ምግባቸውን ፈልገው ስለሚመገቡ።
- ንቦች ለእርሻ ምቹ ባልሆኑ ደረቅና ከፊል - ደረቅ ቦታዎች እንኳ የማር ምርት ይሰጣሉ።
- በባህላዊ ቀፎ የሚጠቀሙ ንብ አርቢዎች፣ ቀፎ ግንባታ የሚያስፈልጉ ቁሶችን በቀላሉ ያገኛሉ።
- ንብ አርቢዎች ባለመሬት መሆን አያስፈልጋቸውም።
- የንብ እርባታ አንዴ ይጀመር እንጂ በራሱ ዝቂ የሚሰፋፋ ሥራ (ቢዝነስ) ነው።

የእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች አመቺነት፣ አንድ ማህበረሰብ ወይም ግለሰብ፣ በጥቂት ግንዘብ የንብ እርባታ እንዲጀምር ያስችለዋል።

ከንብ እርባታ ስድስት የተለያዩ ምርቶችን ማግኘት ይቻላል፣ እነሱም ማር፣ ሰም፣ ፅጌ ብናኝ (ፖለን)፣ የንብ ሙጫ (ፕሮፖሊስ)፣ የማር ወተት እና መርዝ ናቸው።
ከነዚህ ሁሉ ምርቶች መካከል ሳይበላሽ በቀላሉ ለረዥም ጊዜ መቆየትና በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ለገበያ መቅረብ የሚችሉት ማርና ሰም ናቸው።

ማር ንቦች በቀፎአቸው የማር እንጀራ (እንቁራ) ውስጥ የሚያከማቹት ጣፋጭና የሚያጣብት ፈሳሽ ነው። የማር እንቁራ በትናንሽ ነቁሮች (ሴሎች) የተከፋፈለ ሲሆን፣ በነቁር ውስጥ ታሽጉ የሚገኘው ማር በደንብ እርጥበቱ የጠፋ ስለሆን እስከወዲያኛው ሳይበላሽ መቆየት የሚችል ነው። በክፍት ነቁር ውስጥ የሚገኝ ማር እርጥበት የበዛው ሊሆን ስለሚችል፣ በዚህ የተነሳ ከተቆረጠ በአጭር ጊዜ ሊቦካ ወይም ሊበላሽ ይችላል።

ሰም ንቦች ከአጢያቻቸው የሚያመነጩት ሲሆን ማሩንና አዲስ የሚፈለፈሉ ንቦችን (እጮችን) የሚይዝ እንቁራ ለመገንባት ይጠቀሙበታል።

ንብ አርቢ መሆን የሚችለው ማነው?
ማንም ሰው ንብ ማርባት ይችላል፣ ወጣቶችና ሴቶችም ጭምር። ንብ ማርባት የማይችሉት አለርጂክ ያለባቸው ሰዎች ብቻ ናቸው።

የስለሙ ፋድ ማር ፕሬዚዲያ
የቴራ ማድሬ አውታር፣ 58 ንብ አርቢ (አናቢ) ማህበረሰቦችን የሚያካትት ሲሆን፣ 5 የማር ፕሬዚዲያዎች አሉት።
የሳትሬ ማዌ ካኑዶ ኔክታር (ብራዚል)
ውቅሮ ነጮ ማር (ኢትዮጵያ)
መንጪ የእሳተ ጉሞራ ማር (ኢትዮጵያ)
የጋራ ማር (ጣሊያን)
ፖሊሽ ሚድ (ፖላንድ)

የንቦች በረከት

ንብ አስማተኛ ነፍሳት ናት - «ወርቅ» ታመርታለች። ወርቅ የሆነውን ማር!
ማር ጣፋጭና በምግብ ይዘቱ የዳበረ ተፈጥሮአዊ ፈሳሽ ነው! ስለዚህ ይሆን ሰዎች ንብን የሚያረቡት? በትክክል! ነዝር ግን ማር ጣፋጭ ምግብ ብቻ አይደለም። ፕንዘላም ነው።
ማር ለሽያጭ የሚውል ሲሆን፣ ማህበረሰቡ ከሽያጭ የሚያገኘውን ትርፍ የተለያዩ ሽቀጦችን ለመግዛት ሊጠቀምበት ይችላል።

የቀፎ ውስጣዊ ህይወትና አደረጃጀት

የማር ንቦች በአብዛኞቹ በጥንታዊ አገራት የሚገኙ ሲሆን፣ በሰዎች አማካኝነት በሌሎች አህጉሮችም ተራብተዋል።

በርካታ የንብ ዝርያዎች አሉ። ንቦች በቀለም፣ በመጠን እና ከሁሉም በላይ ደግሞ በባህርያቸው ይለያያሉ።

አንዳንድ በአፍሪካ የሚገኙ ዝርያዎች ጠንካራ የዕውደት አዝማሚያ ሲኖራቸው፣ ሌሎች ደግሞ ተናዳፊ ወበኛነት ይጎላባቸዋል። እነዚህ የመሰያ ባህርያት የሚከሰቱት ንቦች ከአካባቢያቸውና ከአየር ንብረቱ ጋር ለመላመድ በሚያደርጉት የረዥም ጊዜ ሂደት ነው።

የህብረንብ አመቃቀር

በሌሎቹ እንስሳት እንደሚታየው ሁሉ፣ ወንድና ሴት ንቦች አሉ። ንግስት (እናት) ንብ እና ሠራተኛ ንቦች በየታ ሴት ናቸው። እያንዳንዱ ቀፎ ውስጥ አንድ ንግስት ንብ እንቁላሎቿን የምትጥል ሲሆን፣ ሁሉም ንቦች የሚፈለፈሉት ከነዚያ እንቁላሎች ነው። በአንድ ቀፎ ወይም በአንድ ህብረንብ ውስጥ የሚገኙት ከአስር እስከ ሃምሳ ሺህ የሚደርሱ ሰራተኛ ንቦች፣ የህብረንቡን ጠቅላላ ስራ ያከናውናሉ። እንደ መቅቱ ሁኔታ ቀፎው ከ300 እስከ 800 የሚደርሱ አውራ (ድንጉላ) ንቦችን ያስተናግዳል።

አሞ ንቦች

አዞንም፣ በአመት ውስጥ ከሚፈራረቁት ወቅቶች ጋር በተዛመደ ሁኔታ፣ ቀፎው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሱ እንቁላሎችን ወይም ያልጠኑ ንቦችን ሊይዝ ይችላል - ብሩድ ይባላል።

በንቁር ውስጥ የሚገኘው ብሩድ ሦስት ነገሮችን ያጠቃልላል። እንቁላሎች በንግስቷ ከተጣሉ በኋላ ለሶስት ቀናት ባህርያቸውን እንደያዙ ይቆያሉ። ከዚያ አሞ (ላርቫ) ይሆናሉ፣ ከፉኛው ቀን እስከ 8ኛው ቀን። ከዚያም ሙሽሬ (ፑ) ይሆናሉ፣ ከ8ኛው ቀን እስከ 21ኛው ቀን ገደማ።



በስተግራ - ንብ ሲያርገበግብ
ከታች - የመስክ ንብ ሰቤት ንቦች ምግብ ሲያስረክብ TROPHALLAXIS

አበባ ቀስመው ወደ ቀፎ የሚመለሱ የመስክ ሰራተኛ ንቦች፣ የአበባ ወለላውን (ኔክታሩን) መገቢያው ላይ ለሚጠብቋቸው የቀፎ ሰራተኛ ንቦች ያስረክባሉ።



የንቦቹ ጉጆ

የህብረንቡ ጉጆ፣ በስድስት ማዕዘን ቅርፅ ነቁር የተገነቡና በቁም የተሰሩ የሰም እንቁራዎችን ያቀፈ ነው። ነቁሮቹ ሁለት ዓይነት ሊሆኑ ይችላሉ። ትንንሽ የሴት ነቁር እና ትልልቅ የወንድ ነቁር። ትንሾቹ ነቁሮች፣ ሠራተኛ ንቦች የሚፈለፈሉባቸው ሲሆን፣ ትላልቆቹ ነቁሮች ውስጥ እሙራ ንቦች ይፈለፈላሉ።

ሁለቱም ዓይነት ነቁሮች፣ በተጨማሪ ንቦቹ የሚሰብስቡትን ፅጌ ብናኝ (ፖለን) እንዲሁም ማርን ለማጠራቀም ያገለግላል። ብዙ ጊዜ ማሩ የሚቀመጠው በቁም በተሸነፈው እንቁራ የላይኛው ክፍል ነው - እንቁላል ደግሞ በመሃለኛው ሥፍራ ይቀመጣል። ሦስተኛ ዓይነት ነቁርም አለ። ንግስት ንቦችን ብቻ የሚያድጉበት ሲሆን የንግስቷ ነቁር ይባላል።

ንቦች እንዴት እንደሚጉለምሱ

ንግስቲቷ በነቁሩ ውስጥ ከምትጥለው እንቁላል ነው ንቦች የሚፈለፈሉት።

የለሙ እንቁላሎች በሴት ነቁር ውስጥ ከተጣሉ ሠራተኛ ንቦች ይፈለፈላሉ።

እንቁላሎቹ በወንዶች ነቁር ውስጥ ከተጣሉና ያልለሙ ከሆነ እሙራ ንቦች ይፈጠራሉ። ከሦስት ቀናት በኋላ እንቁላሎቹ እጭ ይሆናሉ።

እጭ ለተጣሎቹ ሦስት ቀናት በወጣት ንቦች የሚመረት የማር ውተት ይመገባል። ከሦስተኛው ቀን እስከ ስምንተኛው ባሉት ቀናት የፅጌ ብናኝ (ፐሥለንጽነ) እና የማር ውሁድ ይመገባል። ንግስት ንብ የሚሆኑት እጮች ግን የማር ወተት ብቻ እየተመገቡ ያድጋሉ።

ልብ በሉ፣ የሠራተኛ ንብ እጭ፣ የማር ወተት ብቻ እንዲመገብ ከተደረገ ንግስት ንብ ይሆናል።

ንግስቲቷ ንብ በድንገት ከሞተች፣ ንቦች ጥቂት የሠራተኛ ንብ እጮችን ይመርጡና የወተት ማር ይመገቧቸዋል - ወደ አዲስ ንግስት ንቦች ለመቀየር።

እንቁላሉ ከተጣለበት ጊዜ አንስቶ ንግስት ንብ ሙሉ በሙሉ ለማደግ 16 ቀናት ይፈጅባታል። ለአሙራ ንቦች 24 ቀናት ሲፈጅ፣ ለሠራተኛ ንቦች 21 ቀን ያስፈልጋቸዋል። ነቁሩ ሲዘጋ ከእጭ ወደ ሙሽራ (ፑ) የመሸጋገር ሂደቱ ይጀምራል።

ንግስቲቷ

በጥቅሉ፣ በአንድ ቀፎ ውስጥ የምትኖረው አንዲት ንግስት ብቻ ነች። ከሠራተኛ ንብ ስለምትገዝፍና ከአሙራ ንብ ስለምትረዝም በቀላሉ ተለይታ ልትታወት ትችላለች። በተጨማሪም ክንፏ የአካሏን የኋለኛ ክፍል ወይም ሙሉ ህልጷን አይሸፍነውም።

እንደሌሎቹ ንቦች ንግስቲቱ ንብም መናደፊያ አላት፣ የምትጠቀምበት ግን ሌሎች ንግስቶችን ለመግደል ነው። በተወለደች በአጭር ጊዜ ውስጥ ንግስቲቷ ተፃራሪዎቿን በሙሉ ትገድላለች። ከአምስት ቀናት በኋላ ለፍተሻ ያህል ጥቂት በረራዎችን ካካሄደች በኋላ፣ «የጫጉላ በረራ» ታደርጋለች። ከበርካታ አሙራ ንቦች ጋር ግንኙነት የምትፈጽምበት በረራ ነው። የአሙራው ዘር በንግስቲቷ የኋለኛ አካል በሚገኘው ከረጢት ውስጥ ይቀመጣል። ይሄ ዘር ንግስቲቱ የምትጥላቸውን፣ እንቁላሎች ሁሉ ለማልማት ይውላል፣ አሙራ ንብ ከሚሆኑት እንቁላሎች በቀር።

በአንዳች ምክንያት ንግስቲቱ እንቁላሎችን ማልማት ካልቻለች (ከወንዴ ዘር ጋር ካልተገናኘ) እንቁላሎቹ በሙሉ አሙራ ንብ ይሆናሉ። በዚህ ሁኔታ ህብረንቡ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ያልቃል - ምግብ የሚያመጡ ሠራተኛ ንቦች ስለማይኖሩ።

ንብ አርቢ እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲገጥመው ምን ማድረግ እለበት ከገፅ 16 -17 ይመልከቱ

ከጫጉላ በረራው ጥቂት ቀናት በኋላ፣ ንግስቲቱ እንቁላል መጣል ትጀምራለች። በቀን ከ1ሺ በላይ እንቁላሎች ልትጥል ትችላለች። በሆነ ምክንያት ያከማቸችው የወንድ ዘር ፈሳሽ (ስፐርም) ቢያልቅ፣ የአሙራ ንብ ፈልፋይ ትሆናለች።

ንግስቲቱ፣ የህብረንብን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር ፈሮምንስ የተባለ መዓዛ ታመነጫለች። ንግስቲቷ እርጅታ መዓዛውን ማምረት ስታቆም፣ ሠራተኛ ንቦች አሮጊቷን ንግስት በአዲስ ለመተካት የንግስት ንብ መፈልፈያ የንግስና ነቁሮችን ያዘጋጃሉ።

ንግስት አልባ ህብረንብ ውስጥ፣ ሁሉም አድዎች ከሦስት ቀን በላይ ከሆናቸው፣ ንቦቹ አዲስ ንግስት መፍጠር አይችሉም። በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ፣ የአንዳንድ ሠራተኛ ንቦች ማህፀን ይጉለምስና እንቁላል መጣል ይጀምራሉ። ነገር ግን እንቁላሎቹ የለሙ ስላልሆኑ፣ የሚያመርቱት የአሙራውን እንቁላል ብቻ ነው። እነዚህ ሠራተኞች፣ እንቁላል ጣይ ሠራተኛ ንቦች ይባላሉ።

አሙራው ንብ (ድንቡላ)

አሙራ ንብ በቀፎው ውስጥ ምንም ሥራ አይሰራም - ከቀፎ ውጭም የፅጌ ብናኝ ወይም የአበባ ወለላ አይሰበስብም። የአሙራው ንብ ብቸኛ ስራ፣ ከንግስቶች ጋር ግንኙነት መፍጠር ወይም ጥቃት መፈፀም ነው። አሙራ ንቦች ከሠራተኛ ንቦች ይተልቃሉ። ትላልቅ ዓይኖችና ክንፎች ሲኖራቸው፣ በጫጉላ በረራ ወቅት ንግስቲቷን በደንብ ለማየትና ፈጥሮ ለመድረስ ይረዳቸዋል።

አሙራዎቹ ንቦች ከተወለዱ ከዘጠነኝ ቀን በኋላ፣ ለግንኙነት (ለጥቂ) ዝግጁ ናቸው፣ እናም ድንግል ንግስቶችን ፍለጋ ከቀፎአቸው ውጪ መብረር ይጀምራሉ። አሙራዎቹ በጉዞአቸው በርካታ ኪሉ ሜትሮችን የሚያካልሉ ሲሆን፣ ብዙ ጊዜ በተወሰነ ሥፍራ ተከማችተው ይቀመጣሉ።

ከንግስቲቷ ጋር መገናኘት የቻሉ አሙራዎች ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወዲያውኑ ይሞታሉ።

ህብረንቡ አሙራዎችን የሚያሳድገው፣ የተትረፈረፈ ፅጌ ብናኝና የአበባ ወለላ ካለ ብቻ ነው። እጥረት በሚከሰትበት ጊዜ ግን የሚመገባቸው የለም፣ ከቀፎውም ይባረራሉ።

ሠራተኛ ንቦች

አንድ ሀብረንብ፡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሠራተኛ ንቦችን ይይዛል - እስከ 5ሺ፤ የሚደርስ። እነዚህ መካን ንቦች፣ ከአበባ ላይ ፈሳሽ ወለላ የሚቀስሙበት ረዥም ምላስ አላቸው። ንግስቷና አውራው ንብ የሌላቸው በርካታ የአካል ክፍሎች አሏቸው -ሰራተኛ ንቦች። የአበባ ወለላ ቀስመው ወደ ቀፎ የሚያመጡበት ከረጢት፣ እንራቸው ላይ ፅጌ ብናኝ ተሸክመው የሚያመጡበት ቅርጫት፣ ለእንቁራ ግንባታ የሚውል ሰም የሚያመነጩ እጢዎች፣ ለአዋቂና ለንግስት የሚሆን ምግብ የሚያመነጩ እጢዎች፣ እና ከአጥቂ ራሳቸውን የሚከላከሉበት መንደፊያ አሏቸው።

ሠራተኛ ንቦች የሚያከናውኑት ሥራ በዕድሜያቸው ደረጃ ይወሰናል። ከተወለዱ በኋላ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ሳምንታት የቤት ንቦች (House bees) ይባላሉ፣ በቀፎ ውስጥ ያሉ ሥራዎችን ያከናውናሉ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ቀሪ የህይወት ዘመናቸው ከቀፎ ውጪ ባሉ ሥራዎች የሚሰማሩ ሲሆን፣ ቀለብ ሰብሳቢ (Foraging) ንቦች ይባላሉ።

የቤት ንቦች

- ቀፎውንና የማር እንቆራውን ያፀዳሉ
- እጭ ይመገባሉ።
- ንግስቲቷን ይንከባከባሉ
- እንቆራ ይገነባሉ
- ክንፋቸውን በማርገብገብ የቀፎውን መቀት አቀዝቅዘው ይጠብቃሉ
- የአበባ ወለላ፣ ፅጌ ብናኝ እና ውሃ በማር እንቆራ ውስጥ ያከማቻሉ
- የቀፎውን መግቢያ ይጠብቃሉ።

ፅዳት

ስራተኛ ንቦች ከተወለዱ በኋላ በመጀመያ መስራት የሚያስፈልጋቸው የፅዳት ስራ ነው። ቆሻሻና የሞቱ ንቦችን ከቀፎው ያፀዳሉ፣ ንግስቲቷ እንቁላል የምትጥልባቸው ነቁር መዘጋጀታቸውንም ያረጋግጣሉ።

እጭ መመገብ

ከሦስት እስከ አምስት ቀናት ዕድሜ ሲኖራቸው፣ ሠራተኛ ንቦች እጭ መመገብ ይጀምራሉ። ይሄን ጊዜ ነርስ ንቦች ይባላሉ።

ንግስቲቷን መንከባከብ

ቀጣዩ ሥራቸው ንግስቲቱን ንብ መጠበቅና መመገብ ነው። በዙሪያዋ ያሉ ንቦች ሁሉ ሳያቋርጡ በምላሳቸውና በመጠቆሚያቸው (አንቴናቸው) ይነካኳታል - አሷን ለማገልገል።

የበረራ ስልጠና

ታዳጊ ንቦች የመበረር ልምምድና ቀፎአቸውን ለይተው የማወቅ ትምህርት ይጀምራሉ። ስልጠናው ከቀፎአቸው በጣም በጣም ርቀው በ3ኪሎሜትር ዙሪያ እንዲበሩ ይፈቅድላቸዋል፣ ካስፈለገም ከዚያም በላይ ርቀው ይበራሉ።

የእንቅራ ግንባታ (የማር እንጀራ ጋገራ)

የማር እንጀራ እንቆራ ስድስት ማዕዘን ቅርፅ ያላቸው ነቁሮችን የያዘ ሲሆን፣ እጭ ለማሳደግ እንዲሁም ማርና ፅጌ ብናኝ ለማጠራቀም ይጠቅማል። ንቦች በ12ኛውና በ18ኛው ቀናት መካከል ባለው የህይወት ጊዜያቸው፣ ከአካላቸው ሥር ባሉ እጢዎች አማካኝነት ሰም ያመርታሉ። ሰሙ ገና ከእጢያቸው ሲወጣ ፈሳሽ ቢሆንም ትንሽ ቆይቶ እየደደረ፣ ትናንሽ ጠፍጣፋ ቁርጥራጭ ይወጣዋል።
ንቦች እነዚህን ቁርጥራጭ በመንገጭላቸው እና በእግሮቻቸው እያነሱ የማር እንቆራ ይሰሩበታል።

በቀፎው ውስጥ ትክክለኛውን የሙቀትና የትዝታዜ መጠን መጠበቅ

የቤት ንቦች በጣም ትኩረት ከሚሰጧቸው ሥራዎች አንዱ፣ የቀፎውን የሙቀትና የትዝታዜ መጠን መቆጣጠር ነው። ትዝታዜ ሲኖር በቡድን ተጠጋግተው ሙቀት ይፈጥራሉ። ሙቀት ከበብ ደግሞ ጥቂቶቹ ወደ ቀፎው መግቢያ ይሄዱና ክንፋቸውን በማርገብገብ የአየር ኡደት ይፈጥራሉ። ለቀፎው የሚያስፈልገው የሙቀት መጠን ከ33-36 ዲግሪ ሲንትግሬድ ነው።
እጭ ግን በ35 ሲንቲግሬድ መቀመጥ አለበት።

የማር ምርትና ክምችት

ሠራተኛ ንቦች 20 ቀን ገደማ ሲሆናቸው፣ ቀለብ ፈላጊዎች ይሆኑና በየአካባቢያቸው እየበረሩ የአበባ ወለላ ወደ ቀፎ መልሰው ያመጣሉ። ይሄኔ የቤት ንቦች ወለላውን ተረክበው በነቁር ውስጥ ያከማቻሉ፣ ንቦች ክንፋቸውን በማራገብ ለሚፈጥሩት የአየር ኡደት ምስጋና ይግባውና ወለላውም ይደርቃል።

የውሃና የዕጌብናኝ ክምችት

ቀለብ ፈላጊ ንቦች፣ ከአበባ ወለላ በተጨማሪ ውሃ፣ ዕጌብናኝና የንብ ሙጫ ወደ ቀፎ ያመጣሉ - የቤት ንቦችም እነዚህን ንጥረ ነገሮች በደንብ ማስቀመጥ አለባቸው::
እየሩ ሙቅና ደረቅ በሚሆን ጊዜ፣ ቀፎውን ቀዝቀዝ ለማድረግ ውሃው ይጠቅማል:: ውሃ በተጨማሪም ከማርና ከዕጌብናኝ ጋር ተዋህዶ የጉለመሱ እጮችን (ከሦስት እስከ ስድስት ቀን የሆናቸውን) ለመመገብ ይጠቅማል:: ዕጌብናኝ የማር እንቆራ ውስጥ በእጭ ዙሪያ ይቀመጣል::

ጥበቃ

በቀፎው ውስጥ አንዳንድ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ ህብረንቡን ከአደጋ ለመከላከል ሆን ተብለው የተወጠኑ ናቸው::
የአንድ ቀፎ ሰራተኛ ንቦች፣ ከሌላ ቤተሰብ የመጡ ንቦች ወደ ቀፎአቸው እንዳይገቡ ይከላከላሉ:: ያረጁና የታመሙ ንቦችን ይገድላሉ ወይም ከቀፎው ያባርራሉ:: ተፈላጊነታቸው ሲያበቃ አውራ ንቦችን ያስወግዳሉ:: ሌሎች በላተኛ ወይም አዳኝ ነፍሳትም ወደቀፎአቸው እንዲገቡ አይፈቅዱላቸውም:: ቀፎ የመጠበቅ ሃላፊነት፣ሠራተኛ ንቦች ቀለብ ፈላጊ ከመሆናቸው በፊት የሚያከናውኑት የመጨረሻ ስራ ነው:: ጠባቂ ንቦች፣ የቀፎውን መግቢያ ከጠላት የሚከላከሉና ወደ ቀፎው የሚመጡትን የአበባ ወለላና ዕጌብናኝ በሙሉ እየፈተሹ የሚቆጣጠሩ ናቸው::

ቀለብ ፈላጊ ንቦች

ሠራተኛ ንቦች ከ18 እስከ 21ኛው ቀናት መካከል ባለው የህይወት ጊዜያቸው ቀለብ ፈላጊ ይሆናሉ - የማር ወተትና ሰም የሚያመነጩ እጢዎች እየተዳከሙ ሲመጡ ማለት ነው:: አሁን ንቦቹ ለመብረር የሚያስችላቸው ተስማሚ ሁኔታ ላይ ደርሰዋል:: በቀፎአቸው ዙሪያ ካለው ከባቢ ጋርም ተላምደዋል:: በህብረንቡ ፍላጐት መሰረት፣ የአበባ ወለላ፣ ዕጌብናኝ፣ የንብ ሙጫ፣ ወይም ውሃ የመሳብና ወደ ቀፎ የማምጣት ስራን ይመርጣሉ::

የአበባ ወለላ (ኔክታር)

የአበባ ወለላ፣ አበቦች የሚያመነጩት ጣፋጭ ፈሳሽ ነው:: ንቦች አበቦችን በማየትና በማሽተት ለይተው ያውቃሉ:: አንድ ንብ የራሱን ክብደት 85 በመቶ ያህል መሸከም ይችላል::

ውሃ ማምጣት

በጣም አስፈላጊ ከሚባሉ ሥራዎች አንዱ ውሃ ማምጣት ነው:: ንቦች ውሃ ለማገኘት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም ማለት ይቻላል::

እንዲደርቅ ከተሰጣ ልብስ ላይ ወይም ቤት ውስጥ ከእርጥብ ነገር ውሃ መጥጠው ይወስዳሉ:: በመቅሰሚያቸው ብዙ ውሃ ለመውሰድ ጥቂት ደቂቃ ብቻ ነው የሚፈጅባቸው:: ያገኙትን ውሃ ወደቀፎአቸው ካደረሱ በኋላ ተጨማሪ ውሃ ለመፈለግ ተመልሰው ይበራሉ::

ቃኝ (ስካውት) ንቦች

የቅኝት (ስካውት) ንቦች፣ ምግብ የሚገኝበትን ወይም ለአዲስ የቀፎ ግንባታ ተስማሚ ቦታ ለመፈለግ አሰሳ አካሂደው ወደቀፎአቸው በመመለስ፣ መረጃውን ለህብረ - ንቡ ያስተላልፋሉ - የስፍራውን አቅጣጫና ርቀት የሚጠቁም መረጃ በዳንስ ዓይነት እንቅስቃሴ በማሳየት::

ዘራፊ ንቦች

ሁሉም ሠራተኛ ንቦች «ዘራፊዎች» ናቸው - የፈለጉትን ማንኛውንም ነገር ለመስረቅ ስለሚሞክሩ::
ይሄ የሚሆነው በተለይ የመኖ ምንጭ እጥረት ሲኖር ወይም ንቦች አንድን፣ ቀፎ ጥለው ሲወጡ አሊያም የቀፎው ህብረንብ ሲዳከም ነው::

የንብ የአካል ክፍሎች

ንቦች ለሰው ልጅ በጣም ጠቃሚ ናቸው፣ ከሁሉም ነፍሳት የበለጠ። ተግባራቸውን ለመፈፀም የሚያገለግሏቸው ልዩ የአካል ክፍሎች አሏቸው። እስቲ ምን እንደሚመስሉ እንያቸው።
እንደሌሎች ነፍሳት ሁሉ ንቦችም ራስ፣ እምቢያና ሆድ አላቸው።

ራስ

በንቦች ራስ፣ ዓይኖች፣ መጠቆሚያ፣ ማንዲብልስ እና መትሰሚያ እናገኛለን።

ዓይኖች በጠቅላላው ንቦች አምስት ዓይኖች አሏቸው፣ ሁለት ትላልቅና ሦስት ትናንሽ። አውራ ንቦች ትላልቅ ዓይኖች ያሏቸው ሲሆን፣ ማንኑነት ለመፈፀም በሚበሩበት ጊዜ ድንገሏን ንግስት በቀላሉ ለማግኘት ይጠቀሙበታል።

መጠቆሚያ ንቦች ሁለት መጠቆሚያዎች ያሏቸው ሲሆን፣ ለመግባቢያነት ይጠቀሙባቸዋል። ንቦች በየጊዜው እርስ በርሳቸው ይነካካሉ፣ በመአዛ መረጃ ይለዋወጣሉ።

ማንዲብልስ ሁለቱ ማንዲብልስ ነገሮችን ለመያዝ ይጠቅማሉ። ፅጌብናኙን ለመቀላቀልና ሰም ለመስራትም ያገለግላሉ።

መትሰሚያ የአበባ ወለላን፣ ማርንና ሌሎች ፈሳሾችን ለመቅሰም ያገለግላል።

እምቢያ (Thorax)

እምቢያ፣ እግሮችን፣ ክንፎችንና ራስን የሚደግፍ የአካል ክፍል ነው።

እግሮች፣ ንቦች እግሮቻቸው ለመራመድ ቢጠቀሙባቸውም፣ ሌላ ጥቅምም አላቸው። ከፅጌብናኝ ቅርጫት ፅጌብናኝ የሚሰበሰብበት ብሩሽ ያለው እግራቸው ላይ ነው።
አውሬውና ንግስቲቷ የፅጌብናኝ ቅርጫት የላቸውም - ምክንያቱም በቀለብ ፍለጋ ስራ ላይ አይሰማሩም። በንቦች እግር ላይ፣ መጠቆሚያቸውን ለማጽዳት የሚያገለግል ሁለት ከፊል ክብ የሆኑ ቅርፆች አሉ።



ሀ - መትሰሚያ
ለ - መጠቆሚያ
ሐ - ሦስት ተራ ዓይኖች
መ - የማር ወተት እጢ
ሠ - ክንፎች
ረ - መንደፊያ
ሰ - ሰም አመንጪ እጢ
ሸ - ፅጌ ብናኝ መሰብሰቢያ ብሩሽ
ቀ - መጠቆሚያ ጠራጊ
በ - ማንዲብልስ

ክንፍ

ንቦች ክንፋቸውን ለመብረርና የቀፎውን አየር ለማቀዝቀዝ ይጠቀሙበታል።

ሆድ (ሕልፅ)

ሕልፅ ውስጣዊ የአካል ክፍሎችን በሙሉ ይሸል፣ ልብ፣ አንጀት፣ የመተንፈሻና የማስወገጃ ክፍሎች ይገኙበታል።

ለአንድ ንብ አርቢ፣ በተለይ ሰም፣ መዓዛ፣ እና መርዝን የሚያመነጩ ዕጢዎች በጣም አስፈላጊዎች ናቸው።



አውራ ንብ ንግስት ንብ ሠራተኛ ንብ



1ኛ ቀን

4ኛ ቀን

6ኛ ቀን

8ኛ ቀን

20ኛ ቀን

የንብ አርቢ መሳሪያዎች

ማጨሻ

ማጨሻ፣ ከቀፎ ባልተናነሰ መጠን መሠረታዊ ሊባል የሚችል መሳሪያ ነው። ንብ አርቢው (አናቢ) ወደ ቀፎ ሲጠጋ፣ እጅን አጣጥፎ የሚጠብቅ ንብ የለም፣ ንቦች ፊሳቸውን ለመከላከል ይሞክራሉ።

ንቦች በሃይለኝነታቸውና በፀባየኝነታቸው ይታወቃሉ - አናቢ ማጨሻ ሳይጠቀም ፊጽሞ ወደ ቀፎ መሄድ የለበትም።

ማጨሻ፣ ሁለት ክፍሎች አሉት። የብረት የእሳት መያዣ ክፍል ትልቅ መሆን አለበት፣ ቢያንስ ለ30 ደቂቃ የሚቀጣጠል ደረቅ ነገር መያዝ የሚችል። ሌላው ክፍል አየር ወደማጨሻው የሚያራግብ ወናፍ ነው፣ በሞድስ ማውጫው ጭስ እንዲወጣ የሚያደርግ። ነዳጅ ወይም ዘይት ነክ ነገሮች ማጨሻው ውስጥ መፍሰስ የለባቸውም፣

እንጨት፣ ደረቅ ቅጠል፣ ኩበት ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ደረቅ ነገሮች ብቻ ናቸው መቀጣጠል ያለባቸው። ተዝተዝ ያለና ነዳድ ጭስ ንቦችን ያረጋጋቸዋል፣ ስለዚህም አናቢው ሳይረበሽ ሥራውን ያከናውናል።

ቢላ (መሮ)

ቀፎውን ለመክፈትና እንቆራዎችን ለማውጣት ያገለግላል። ለክህሳዊ ቀፎ፣ ቢላ በቂ ሊሆን ይችላል። በማር ቆረጣ ወቅት ቢላ በጣም አስፈላጊ ነው። የማር እንቆራዎች ከቀፎው አካል ወይም ግድግዳ ጋር አልያም እርስበርስ ሲጣበቁ፣ በቢላ ማለያየት ይቻላል።



ልብ በሱ!
ጭሱ ሁልጊዜ ቀዝቃዛ መሆን አለበት



የንብ ብሩሽ

ንቦችን ከሣር እንቅራው ላይ ለማራገፍና በቀስታ ወደ ኢቃ ወይም ቀፎው ለመክተት ያገለግላል። ቅጠል ያላቸው የተክል ቅርንጫፎች ወይም የእንስሳት ላባዎችም እኩል አገልግሎት ይሰጣሉ።

መመገቢያ

ብልቃጥ ወይም በሣር እንቅራ ቅርፅ የተሠራ ልዩ ፍሬም ሊሆን ይችላል። ዘመናዊ አናቢዎች፣ በንቦች እንዳይነደፉ መከላከያ ልብስ ይጠቀማሉ። ከመከላከያ ልብሶች አንዱ ቱታ ነው፣ (ነጣ ያለ ቢሆን ይመረጣል።) በተጨማሪ የእጅ ጓንት፣ ዓይነርግብና ቦት ጫማ ይጠቀማሉ - አናቢዎች።

የአናቢ ቱታ

ቱታው፣ ከጭንትላት፣ ከእጆችና እግሮች በቀር ጠቅላላ ሰውነትን የሚሸፍን ነው። ዓይነርግቡ ፊትን፣ ጭንትላትንና አንገትን ለመሸፈን በጣም አስፈላጊ ነው። ጓንቶች የአናቢው እጆችና ዣቶች በንብ እንዳይነደፉ የሚከላከል ሲሆን፣ ለስላሳና የሚታዘዝ መሆን አለበት። ከፐላስቲክ የሚሰሩ ጓንቶች ተመራጭ ናቸው። ቦት ጫማው እግሮችን ከመነደፍ ይከላከላል።

ይሄ ህብረንብ ንግስቲቱን አጥቷል። ምናልባት ዝቮ ንግስቲቷን በአዲስ ንግስት ተክተዋት ሊሆኑ ይችላል።
የንግስት ንብ መፈልፈያ ኑቋሮቹን ማየት እንችላለን። በስተቀኝ ያለው ኑቋር፣ ክዳን ከፍት ነው። አዲሲቷ ንግስት የተወለደችው እዚያ ውስጥ ነው።
አዲሲቷ ንግስት እቻትና፣ ረዥሙ ሆዷ (ሀልጇ) በእርግጥም የለማች መሆኗንና እንቁላል ለመጣል ዝግጁ እንደሆነች ያሳያል። በጥቂት ቀናት ውስጥ አዲስ እንቁላል መጣሷን ማየት እንችላለን፣ እናም ሁሉም ነገር በአግባቡ እየተከናወነ ስለመሆኑ እርግጠኞች እንሆናለን።
ሁልጊዜም ግን ነገሩ እንዲህ ይሆናል ማለት አይደለም። ንግስቲቷ ልትሞት ወይም የጫጉላ በረራዋን ስታካሂድ በመፍ ልትበላ ትችላለች። አሊያም በእርጅና ትሞታለች።
በእንዲህ ያሉት ኢጋጣሚዎች፣ ህብረንቡ አዲስ ንግስት ለማሳደግ የሚጠቅም ጨቅላ እጭ ከሌለው ንግስት አልባ ይሆናል። ንግስት አልባ ህብረንብን መለየት በጣም ቀላል ነው - ንብቹ ረዥምና የጉላ ድምጽ ያሰማሉ - ጥዝዝ የሚል። የሚያሰቅሱ ነው የሚመስሉት። በዚያ ላይ እረፍት የለሽ ናቸው።
:

ንብ አርቢ እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥመው ምን ማድረግ ይችላል?



የቀፎዎች አደያደዝ

የቀፎ ስፍራ

ቀፎዎች ያለብት ሥፍራ፡ ንቦች የአበባ መለላ የሚቀስሙባቸው አፅዋቶችና ውሃ በቀላሉ የሚያገኙበት መሆን አለበት። ስፍራውን ከሌቦች መጠበቅ ያስፈልጋል፡ ቀፎው ላይ የባለቤቱን ስም ወይም ፊርማ ለምልክት ማስፈር ጥሩ ዘዴ ነው።

ተመራጩ ሥፍራ

ለቀፎ ተመራጭ የሚባለው ስፍራ

ንቦች ሰዎችን እንዳይረብሹ ከመኖሪያ አካባቢ የራቀ መሆን አለበት።

የአበባ መለላ ያላቸው ዕፅዋቶች የበዙበት ሊሆን ይገባል።

ለክትትል የሚያመች

ውሃ ባካባቢው ያለ

ከነፋስ የተከለለ

ከሌቦች የተጠበቀ

የቀፎዎች አደራደር (አቀማመጥ)

ዘመናዊ ቀፎዎች ከመሬት ከፍ በሚያደርጋቸው ድጋፍ ላይ መቀመጥ አለባቸው፡ ጉንዳንን ከመሳሰሉ ነፍሳት እንዲጠበቁ።

ንቦችን ቀፎ ውስጥ ለማስገባት

ቀፎዎችን በአራት የተለያዩ መንገዶች በንቦች መሙላት ይቻላል።

የዕውደት መንጋውን በመያዝ

የጫካ ንብ መኖሪያ ፈልጉ ወደ ቀፎ በማሻገር

ሀብረንብ በመግዛት

ቤተሰቦችን በመክፈል

መንጋውን ለመያዝ

አንድ ጊዜ መንጋው ንብ ከታየ፡ በመጀመሪያ መደረግ ያለበት መኖሪያ ቀፎ ማዘጋጀት ነው። ዘመናዊ ቀፎ የምንጠቀም ከሆነ ከመነሻው የማር እንቆራ የተሰራለት ወይም በሰም የማር እንቆራ የተዘጋጀለት መሆን አለበት።

ከዚያም መንጋውን እንዴት መያዝ እንደሚችሉ ማስብ ይኖርብዎታል - ከተቻለ የአንድ ሰው እርዳታ ቢታከልበት ጥሩ ነው።

ዝንጅትዎን ካጠናቀቁ፣ የንቦቹ መንጋ የተከማችበት የዛፍ ቅርንጫፍ ተቆርጦ፣ ቀፎ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ ይቻላል። ቅርንጫፉን መቁረጥ ካስቸገርዎት፣ ንቦቹ እንዳይበሩ በውሃ ማርጠብና በቀጥታ ወደቀፎው ውስጥ ማራገፍ ይቻላል።

ንቦች ያሰፈሩበት የዱር ጉጅ ማግኘትና ወደ ቀፎ ማዛወር

ንቦችን ከሰፈሩበት የዱር ጉጅ ወደ ቀፎ እንዲዛወሩ ሲደረጉ በእጅጉ ፀቦኛ (ንውጠኛ) ናቸው። ለዚህም ነው፣ ወደ ንቦቹ ጉጅ ከመጠጋትዎ በፊት፣ በቁታና በአይነ ርግብ ራስዎን መከላከል የሚኖርብዎት። በማጨሻ ብዙ ጭስ መፍጠርም ያስፈልጋል።

ነቁሮቹን ሳይሰብሩ በቢላዋ ኮቮረጡ በኋላ፣ አንድ በአንድ ቀጫጭን ሽቦዎች ከተወጠሩበት ፍሬም ጋር እሰሩት (የሰም እንቆራው ሳይነካ) ዕድለኛ ከሆኑ፣ ንግስቷንም ለማዛወር ይችላሉ። ካልሆነ ግን፣ ንቦቹ የንግስት ነቁር ይገነቡና አዲስ ንግስት ንብ ትወለዳለች።

ሀብረንብ የተዛመረበት ቀፎ፣ ከመጀመሪያው ቦታ ቢያንስ በ3 ኪሉ ሜትር እንዲርት መደረግ አለበት። አለበለዚያ ግን አዲስ የተወለዱ ንቦች ብቻ ናቸው በቀፎው የሚቀሩት።

ሀብረንብ መግዛት

ይሄ ሁሉንም ነገር ያቃልላል። ባዶ ቀፎ ይዘው ወደ ሻጩ መሄድ ብቻ ነው የሚያስፈልግዎት። ነቁሮቹ ወደ አርስዎ ቀፎ ሲዛወሩ ንግስቷ ንብ መኖሯንም ያረጋግጡ።

ሁለት የንብ ቤተሰብ ለመፍጠር ሀብረ ንብን መክፈል

ዘመናዊ ቀፎዎች ካልዎት፣ ለሁለት በመክፈል ቁጥራቸውን መጨመር ይቻላል። ግን ይጠንቀቁ። ለሁለት መክፈል የሚችሉት ቀፎዎቹ ቢያንስ ባለ ስምንት ነቁር ከሆኑ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በቂ የመኖ ምንጭ ማበቡን ማረጋገጥ ያስፈልግዎታል።

ቀላሉ ዘዴ፣ እራት ነቁሮችን በማውጣት ወደ አዲሱ ተደራቢ ባዶ ቀፎ ማስገባት ነው። ነቁሮቹ፣ የሚፈለፈሉ እንቁላሉች ወይም በጣም ጨቅላ እጮችን እንደያዙ እንዲሁም የእነዚህን ሙቀት መጠበቅ የሚችሉ በቂ ጉልምስ ንቦች እንዳሉ ያረጋግጡ።

የተደራቢው ቀፎ ሰራተኛ ንቦች፣ የንግስት ንብ መፈልፈያ ነቁር ይገነባሉ - አዲስ ንግስት ንቦች እንዲወለዱ። በነባሩና በተደራቢው ቀፎ ውስጥ ያሉት ባዶ ቦታዎች በሰም የመሰረት ነቁር መሞላት አለባቸው።

ከአንድ ወር ገደማ በኋላ፣ ሁለቱም ቀፎዎች ውስጥ የሚፈለፈሉ እንቁላሉች መኖራቸውን ያረጋግጡ።

የቀፎ አደራረቡ ውጤታማ እንዲሆን፣ አውራ ንቦች መኖራቸውን ማረጋገጥ ይኖባል። የመኖ ምንጭ እጥረት ባለበት ወቅት፣ የንብ ቤተሰብን ለሁለት ከመክፈል መቆጠብ ያስፈልጋል።

አዲሱ የንብ ቤተሰብ፣ ከመጀመሪያው ቀፎ ቢያንስ በሶስት ኪሉ ሜትር ርቆ ቢቀመጥ ይመረጣል። ይህ የማይቻል ከሆነ ግን፣ አዲሱ ሀብረ ንብ በንቦች ቁጥር የሚበልጥ መሆን አለበት፣ ምክንያቱ በርካታዎቹ ወደ ድሮው ቀፎ ተመልሰው ይሄዳሉ።

የንብ ቀፎ አያያዝ

ንቦች ወደ ቀፎ ከገቡ በኋላ፣ አንቢው ቀፎዎቹን እንዴት እንደሚከታተል መማር አለበት።

በአመቱ የተለያዩ ወቅቶች የንብ ቀፎ ውስጥ ምን እንደሚከናወን ቢከታተል ይበልጥ ስኬታማ ይሆናል።

የንብ ቀፎን መመርመሪያ መንገድ

ቀፎውን ለመክፈት ሲፈለግ በማጨሻ አማካኝነት ወደ ንቦቹ ጭስ መልቀት ያስፈልጋል። የቀፎውን ክዳን ካነሱ በኋላ ወደ ውስጥ ማጨስና ነቁጠቹን በቢላዋ አገፍ ማውጣት።

የሚፈለፈሉ እንቁላሉች አቀማመጥን፣ የማር ሁኔታንና የንግስት ንብ መፈልፈያ ነቁጠች ካሉም ይመልከቱ። እነዚህ ነገሮች ካሉ ቀፎው ለፅውደት እንደተዘጋጁ የሚጠቁሙ ናቸው።

በንብ ከመነደፍ የሚከላከሉበት መንገድ

ንቦች ይናደፋሉ፣ እናም ሊገድሉ ይችላሉ። አለርጂ ያለባቸው ሰዎች ከንቦች መራቅ ይኖርባቸዋል። ንቦች ሲናደፉ፣ በቆዳ ላይ ተሰክቶ የሚቀረው እሾህ፣ ሌሉች ይበልጥ ፀቦኛ ንቦችን የሚጣራ ሽታ ያመነጫል። ተመራጩ ነገር እሾሁን በጥፍር በማከክ ማውጣትና በተጉዳው አካባቢ ጭስ በመልቀት ሽታውን መበረዝ ነው።

ንቦች በጣም የሚናደፉት መቼ ነው?

ሞድስ ሳይጠቀሙ የቀፎውን ክዳን ከከፈቱ
ብርዳማ፣ ዝናባማ ወይም ነፋስ ያየለበት ጊዜ ከሆነ
ቀፎውን ከነቀነቁ ወይም በሌላ ሁኔታ ከረበሹት
ጥቁር ልብስ ካደረጉ
ነቁር እንደያዙ ድንገተኛ ንቅናቄ ካደረጉ
ከፈሩፅ ፍርሃት ላብን ያስከትላል። ንቦች ላብን ማሽተት ይችላሉ፣ እናም ይረብሻቸዋል።

ፍሬሞች የማዘጋጀት ዘዴ

ፍሬሞች፣ በተሟጭን የብረት ሽቦዎች የተጠናከሩ መሆን አለባቸው። የመስሪት ንቁር ከሽቦቹ ጋር ነው የሚጣበቀው።
የመስሪት ነቁር ከፍሬሙ ጋር የሚያያዘው፣ በሽቦዎቹ ላይ በጣም ትኩስ ብረት በማሳለፍ ነው፣ ሽቦዎቹ በሰም የተሰራውን የመስሪት ነቁር ሰርስረው ይይዙታል። ወይም ደግሞ የቀለጠ ሰም በብረት በሽቦዎቹ ላይ ማፍሰስ ይቻላል። የመሰሪት ነቁር የያዙ ፍሬሞች ቀፎ ውስጥ የሚገቡት ንቦች የእበባ ወለላ በሚሰበስቡበት ጊዜ መሆን አለበት፣ አለበለዚያ ነቁር አይፈጠርም።

ሁለት ህብረ ንቦችን የማዋሃድ ዘዴ

አንዳንዴ ሁለት ህብረ - ንቦችን ማዋሃድ አስፈላጊ ነው። ከሁለት ቀፎ አንዱ ንግስት ንብ አልባ ከሆነ ወይም ሁለት ህብረ ንቦች ተጻክመው ማር የማያመርቱ ሲሆኑ፣ ሁለቱን ማዋሃድ አስፈላጊ ይሆናል፣ ብዙ ንቦች ያሉት ጠንካራ ህብረ - ንብ ማር ያመርታልና። ሁለት ደካማ ህብረ ንቦች ለማዋሃድ፣ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ብዙም ፍሬያማ ያልሆነችውን ንግስት ንብ መግደል ተመራጭ ነው። ሁለቱ ላይገድሏት ይችላሉ። ንግስት ንቦች በህይወት ከቆዩ፣ ሌሎች ንቦች እንጂን ይገድሏታል፣ ግን ደካማዋን ላይገድሏት ይችላሉ።
ህብረንቦችን ሲያዋህዱ፣ የንቦቹ ጠረን ተመሳሳይ እንዲሆንና እርስ በርስ እንዳይገዳደሉ በእንዳች መአዛማ ንጥረ ነገር ንቦቹን ማውናበድ ጥሩ መላ ነው።
ሁለት ህብረንቦችን ለማዋሃድ ንቦች በረራ የሚያቆሙበት የአመሻሽ ጊዜ ከሁሉም ጊዜ በላይ ተመራጭ ነው። የስርቆት ስጋትን ይቀንሳል።
ህብረንቦቹ ከመዋሃዳቸው በፊት፣ በሚገባ በጭስ መታጠን አለባቸው። ያስታውሱ፣ ባዶ የቀረው ቀፎ ከአካባቢው ካልተነሳ፣ ብዙ ንቦች ወደ ድሮው ቀፎአቸው ተመልሰው ለመግባት ይሞክራሉ።

የንግስቷን ንብ ጥንካሬ የሚያውቁበት ዘዴ

ንግስቷ ንብ የሁሉንም ጉበዝ እናት ነች። ስለዚህም ንቦች ንግስት፣ ብዙ እንቁላሉችን የምትጥል ነች።
ብዙ እንቁላል ሲጣል ብዙ እጭ ይፈለፈላል ማለት ነው። በዚህም ጥሩ የማር ምርት የሚሰጥ የንቦች ብዛት ይኖራል።

ስርቆት የሚከላከሉበት መንገድ

ንቦች በደመነፍስ ማንኛውንም ጣፋጭ ነገር በመስብሰብ ለችግር ጊዜ ያከማቻሉ። ይሄ የንቦች ደመነፍስ በጣም ጠንካራ በመሆኑ፣ አንዳንዴ ደከም የሚል ህብረ-ንብ ከሰፈረበት ቀፎ ማር ይሰርቃሉ።
አንድ ህብረ ንብ ማር ከቀፎው ሲሰረቅ፣ ብዙ ንቦች በቀፎው ዙሪያ እየበረሩ በፍጥነት ሲዝኩና ሲወጡ ይታያል። ዘራፊዎቹ ንቦች በጣም ደንባራ ናቸው፣ አንዳንዴም በማር እየተጨማለቁ ፀጉራቸው ስለሚነቃቀል ቀለማቸው ጠቆር ብሎ ይታያሉ። በጣም ፀበኛ ስለሚሆኑም አንዳንዴ ሰዎችንና እንስሳትን ይናደፋሉ።
ስርቆትን ለመከላከል፣ የሙኖ ምንጭ እጥረት በሚኖርበት ጊዜ ቀፎዎችን ከመክፈት ይቆጠቡ። ቀፎዎችን ሲጉበኙ፣ ነቁጠኞችንና ማርን ከፍት አይተው። የደከመ ህብረ - ንብ የሰፈረበት ቀፎ ላይ ያሉ መውጫና መግቢያ ቀዳዳዎችን በመቀነስ፣ አንድ ጠባብ ቀዳዳ ብቻ ያስቀሩ። የመኖ እጥረት በሚኖርበት ወቅት፣ ለንቦች ምትክ መኖ መስጠት ያለብዎት ምሽት ላይ ንቦች በማይበርሩበት ጊዜ ብቻ ነው።



ባህላዊና ዘመናዊ ቀፎዎች

ባህላዊ ህብረ - ንብ

ባህላዊ ህብረ ንብ ከዘመናዊው ያነሰ ማር ነው የሚያመርተው። ይህም የተሻለ ምርት ወደሚያስገኝ የህብረንብ አያያዝ ለመሸጋገር ጥሩ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ባህላዊ ቀፎ

ባህላዊ ቀፎ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በመላው አለም ጥቅም ጥቅም ላይ ሲውል ቆይቷል። እንደያአካባቢው ሁኔታ ከተለያዩ ቁሶች ሊገነባ ይችላል። ከሳር፣ ከሸክላ ወይም ከእንጨት የተሰራ ሊሆን ይችላል።

በቀፎዎቹ ውስጥ ንቦች ጉቋር ይገነባሉ፣ አናቢው በቢላዋ ወይም በመሮ ጉቋሮቹን እየቆረጠ ይሰበስባል።

ዘመናዊ ቀፎ

ዘመናዊ ቀፎ፣ ሎራንዞ ሎራን ላንግስትሮዝ በቀፎ ውስጥ የቦታ አወቃቀር ላይ ካደረገው ምርምር በመነሳት የተገኘ ውጤት ነው። ሁለት ጉቋሮች ተለያይተው እንዲቆዩ በመካከላቸው ቢያንስ ከ7-9 ሚሊ ሜትር ገደማ ርቀት ሊኖር እንደሚገባ በምርምር ደርሰበታል። ከዚህ ግኝት በኋላ ሎራንዞ፣ አሁን በመላው አለም ጥቅም ላይ የዋለውንና ላንግስትሮስ ቀፎ በባል በሰሙ የሚጠራውን ቀፎ ፈጠረ። ቀፎው በተፈጥሮ እንደሚያደርጉት ንቦች በትይዩ አወቃቀር ጉቋር የሚሰሩበት አስር የእንጨት ፍሬሞች አሉት። ከባህላዊው ጋር ሲነፃፀር፣ ዘመናዊው ቀፎ፣ በቀላሉ ንቦችን ሳይረብሹ ሊወጡና ሊገቡ በሚችሉ ፍሬሞች ብልጫ አለው። ማር ሲደርስ እንቅራው ሳይሰባበር ማጣራት ይቻላል።

በላንጫስቶዝ ቀፎ የእሮ ክፍልንና የምግብ ማከማቻ ክፍልን፣ በንግስት ንብ ማገጃ መለያየት ይቻላል። ተለክቶ ከብረት የተሰራ፣ የንግስት ንብ ማገጃ፣ ንግስት ንብ እንዳታልፍና በእሮ ክፍል እንድትቆይ የሚያገድ ሲሆን፣ ከንግስት ንብ በመጠን እኩል ያሉት ሰራተኛ ንቦች ከአንድ ክፍል ወደ ሌላው ያለችግር መንቀሳቀስ የሚችሉበት ነው።

የዘመናዊ ቀፎ ብልጫ

- እንቁራዎችን በቀላሉ ማውጣትና ጉዳት ሳይደርስባቸው መመልከት ይቻላል።
- ቀፎዎችን በቀላሉ ከቦታ ቦታ ማጓጓዝ ይቻላል።
- እንቁራዎችን በማሽከርከር ማሩን ማውጣትና ሳይበላበሩ ወደ ቀፎ መመለስ ይቻላል።
- ይበልጥ የጠራና ንፁህ ማር ያስገኛል።
- እንቁራዎች ከአንድ ቀፎ ወደ ሌላ በማከፋፈል የቀፎዎችን ቁጥር በቀላሉ እጥፍ ማድረግ ይቻላል።
- የንብ መንጋን በቀላሉ ቀፎ ውስጥ ማስገባት ይቻላል።

የዘመናዊ ቀፎ ጉድለቶች

- ዘመናዊ ቀፎ በዋጋ ውድ ነው
- ቀፎውን ለመገንባት መሳሪያዎችና እንጨት ያስፈልጋል።
- እንጨቱ ተቆርጦ የቆየና የመጠጠ መሆን አለበት።
- ፍሬሞች በሽቦ መጠናከርና በሰም የመሰረት ንቁር የተያያዘላቸው መሆን አለባቸው።
- ከእንቁራዎቹ ማር ለማውጣት ማሽከርከሪያ ያስፈልጋል።



ዘመናዊ ቀፎ



ይጠንቀቁ!
የእጭ ክፍል ውስጥ ያለው ማር መውጣት የለበትም::

ንቦችን የመመገብ ዘዴ

ንቦች ማር ወይም በውሃ የተጠበጠበ ስኳር ሊመገቡ ይችላሉ::

ለንቦች ምገብ የሚቀርበው በባልዲ ወይም እንደ ፍራም ቀፎ ውስጥ በሚገባ መመገቢያ ሊሆን ይችላል:: የመኖ ምንጭ እጥረት በሚኖርበት ጊዜ ወይም ዘግረ - ንብ እንደ አዲስ በተመሰረተበት ጊዜ ንቦችን መመገብ ይቻላል::

ለንቦች ውሃ የሚቀርብበት ጊዜ

ንቦች በቅርበት ውሃ የሚያገኙበት መንገድ መኖር አለበት:: ውሃ መሰረታዊ ነው፣ ማርን ለማብሳሳት፣ እርሟችን ለመመገብ እንዲሁም መቀት ሲበረታ ቀፎውን ለማብረድ ይጠቅማል:: በቅርበት የውሃ ምንጭ ከሌለ እናቢው በውሃ የተሞላ የውሃ መያዣ በማቅረብ፣ ንቦች ሳይሰጥሙ መጠጣት እንዲችሉ ተንሳፋፊ እንጨቶችን ማስቀመጥ ያስፈልጋል::

አሁን የማር እንቁራዎቹን ከቀፎ ካወጣን በኋላ፣ የምንፈልጋቸውን ሁለት ምርቶች ማርንና ሰምን የምናጣራበት መንገድ ማሰብ ይኖርብናል::

ፅጌ ብናኝ (ፖለን) እና እጭ የያዙ ንቁሮች ከቀፎ እንዳይወጡ መጠንቀቅ ያስፈልጋል::

ማር ብቻ የያዙ የማር እንቁራዎች የማጣሪያ ከረጢት የተዘጋጀለት የማር መጭመቂያ ውስጥ ማስገባት ይቻላል::

እየተጣራ ወደ ማር መያዣ ይንቆረቆራል

የማር የማምረትና ከእንቁራ የማላራት ዘዴ

የማር መቁረጥና ማላራት

ባህላዊ ቀፎ ስንጠቀም፣ የማር እንቁራ በቢላዎና በኩል እንጨት እየተቆረጠ ይወጣል።

ማሩን ከሰም ለመለየት፣ እንቁራው ወደ መጭመቂያ ይመሰዳል። ከዚያም በጣም ስስ በሆነ የናይለን ሸማ ከረጢት እየተጣራ ወደ ማር መያዣ ይጠራተማል።

ዘመናዊ ቀፎ ስንጠቀም፣ ከቀፎው የምንብ ማከማቻ ክፍል በማር የተሞላ እንቁራዎችን ማውጣት ይቻላል፣ ማር በንቁር ውስጥ በሚታሸግበት ጊዜ ቀፎው ከተከፈተ በኋላ ልክኛ ጭስ በመጠቀም እንቁራዎቹን ያውጡ፣ በብሩሽ ንቦችን እያራገፉ እንቁራዎቹን በማስቀመጫ ውስጥ ያኑሩ፣ ከዘራፊ ንቦች ለመከላከል እንቁራዎቹን ወደቤት እንደመሰዱ፣ ከእሽጉቹ ንቁሮች ላይ ሰሙን ያላቅቁና እቁራውን በማሽከርከሪያ ውስጥ በማስገባት ማሩን ያጣራሉ።

የሰም ቅሪት ይበልጥ ለማስወገድ፣ በማጣሪያ መንፊት በመጠቀም፣ ማሩን በመያዣ ያጠራቅሙ። ከዚህ በኋላ ነው በማሸጊያ ተደርጉ ለሽያጭ የሚቀርበው።

ማር ከቀፎ ሲወጣ፣ ትክክለኛ የእርጥበት መጠን እንዳለው ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የደረሰ ማር የሚለው ይህ ደረጃ የሚረጋገጥበት ቀላሉ መንገድ፣ የማር ጠብታን በአውራ ጣትና በመሀል ጣት መጭመቅ ነው።

ጣቶችዎን ሲያላቅቁ፣ ማሩ የማጣበቅ ባህሪ ከታየበት ትክክለኛው ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት ነው። የማጣበቅ ባህሪ ከሌለው፣ ፈሳሽነት የበዛበት ስለሆነ ገና እርጥበቱ መጠየ የሚልበትን ሂደት ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ጊዜ ይፈልጋል።

የሰም አመራረት





ተመራጩ ዘዴ፣ በፀሐይ ሃይል የሚሰራ የሰም ማጣሪያ መጠቀም ነው፣ ማጣሪያው ከላይ መስተዋት ያለው የብረት ሳጥን ነው። ሰሙን ሳጥኑ ውስጥ አስገብቶ ፀሐይ ላይ ማስቀመጥ ብቻ ነው፣ ሰሙ እንዲቀልጥ። በብዛት ጥቅም ላይ የሚውለው ዘዴ በሙቅ ውሃ የማጣራት ዘዴ ነው። በእንስራ ውስጥ ውሃና ሰም በመጨመር እሳት ላይ ይጥዳሉ። ሰሙ ከቀለጠ በኋላ፣ እንስራውን ከእሳት አውርደው በዝግታ እንዲቀዘቅዝ ያስቀምጡታል። በማግስቱ ሰሙ ለብቻ ጠጣር ሲሆን፣ ከእንስራው ማውጣት ይችላሉ።

የሰም አመራረት

ተመራጩ ዘዴ፣ በፀሐይ ሃይል የሚሰራ የሰም ማጣሪያ መጠቀም ነው፣ ማጣሪያው ከላይ መስተዋት ያለው የብረት ሳጥን ነው። ሰሙን ሳጥኑ ውስጥ አስገብቶ ፀሐይ ላይ ማስቀመጥ ብቻ ነው፣ ሰሙ እንዲቀልጥ። በብዛት ጥቅም ላይ የሚውለው ዘዴ በሙቅ ውሃ የማጣራት ዘዴ ነው። በእንስራ ውስጥ ውሃና ሰም በመጨመር እሳት ላይ ይጥዳሉ። ሰሙ ከቀለጠ በኋላ፣ እንስራውን ከእሳት አውርደው በዝግታ እንዲቀዘቅዝ ያስቀምጡታል። በማግስቱ ሰሙ ለብቻ ጠጣር ሲሆን፣ ከእንስራው ማውጣት ይችላሉ።

ንግስት ንቦችን ማሳደግ

ንግስት ንቦችን የማሳደግ ዘዴ መማር፣ የንብ ቀፎዎችን በፍጥነት ለማብዛት ይጠቅማል። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ሰራተኛ ንቦች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ከሰራተኛ ንብ እጭ ንግስት ንብን ማሳደግ እንደሚችሉ አይተናል። አናቢው፣ ይህንን የሰራተኛ ንቦች ተፈጥሮን በመጠቀም ንግስት ንቦችን ማሳደግ ይችላል።

የምትረባ ንግስት ንብን መምረጥ

ተጨማሪ ንግስት ንብ በማሳደግ ተጨማሪ ህብረ ንብ ለማርባት፣ ሦስት ነገሮች ታሳቢ መሆን አለባቸው፣ የንቦች ብዛት፣ የንቦች እርባታ እና የማር ምርታማነት።

በመጠባበቂያ ኑቁር ንግስት ንብ ማሳደግ

ንግስቷ ንብ ከቀፎ ከተወሰደች፣ ሰራተኛ ንቦች ንግስት አልባ መሆናቸውን በማወቅ፣ ለመጠባበቂያ የንግስት ንብ መፈልፈያ ኑቁር መገንባት ይጀምራሉ። ከአንድ ሳምንት በኋላ፣ ኑቁሮቹ ሲታሸጉ ቆርሞ ማውጣት ይቻላል። ኑቁሮቹ እንዳይጎዱ ከነአንቁሩ መቆረጥ አለበት።
በዚህ ሁኔታ የምታድገው ንግስት ንብ በሊላ ቀፎ መቀመጥ አለባት፣ ከእጭ አንቁራና ከማር አንቁራ ጋር። ወቅቱ ሲዝያድድ አንድ ተጨማሪ አዲስ ህብረ ንብ ፈጠሩ ማለት ነው።

ብዙ እናት ንቦችን ለማሳደግ፣ የሚከተሉትን ማከናወን ያስፈልጋል።
- ምን ያህል የእናት ንብ መፈልፈያ ኑቁሮች እንዳሉ ይቁጠሩ።
- ለአዲሶቹ ህብረ - ንብ ቀፎዎችን ይዘጋጁ
- አዲሶቹን ቀፎዎች በሁለት ወይም በሶስት የእጭ አንቁራና የማር አንቁራ ያሟሉ
- የድሮውንና አዲሶቹን ቀፎዎች ቢያንስ በሶስት ኪሎሜትር ርዝመት ያራርቁና ተጨማሪ ንቦችን ያስገቡ
- ከስድስት ቀን በፊት የተዘጋጀውን የንግስት ንብ መፈልፈያ ኑቁሮችን ይቁረጡ
- የንግስት መፈልፈያ ኑቁሮቹን ኢያንዳንዳቸው በአዲስ ቀፎዎቹ ውስጥ ከአንቁራ ጋር በትንሽ ቅርንጫፍ ያጣብቁ
- ከ15 ቀናት ገደማ በኋላ፣ አዲሷ ንግስት ንብ እንቁላል መጣል መጀመሯን ያረጋግጡ።


በጋራ የቆየንበት የጋራ ጉዞ እየተጠናቀቀ ነው።
ድንቅ ገድል የሆነውን የአናቢነትና የማር አመራረትን እንዲጀምሩና እንዲያሻሽሉ የሚጠቅሙ አንዳንድ መረጃዎችንና ፍንጮችን ልንሰጣም ሞክረናል።
በንብና በቀፎ አያያዝ ላይ ያሉ በርካታ ሙስብስብና ብዙ ቁምነገሮችን ለመዳሰስ አንድ መጽሐፍ በቂ አይደለም።
ይህንን ሁሉ ጥበብ ለመጠበብ፣ የንብ አርቢ ያልተንደለ ትጋትና የሬቀቀ የማስተዋል መንፈስ መላኝ ናቸው።
ለስራም ታላቅ ስኬታን እንመኛለን።

ማስታወሻ

ማስታወሻ

ማጠቃለያ

ከፍተኛ ጥራት ያለው ማርን ለማምረት መከተል የሚገባዎትን ዋና ዋና የአሰራር ዘዴ በአጭሩና ቀለል ባለ መንገድ ለማሳየት ሞክረናል። ይህ መመሪያ የንቦችን አስደናቂና የተወሳሰበ አለም ለመመርመር እንደመነሻ የሚያገለግል የመጀመሪያ መሳሪያ ነው።
መመሪያው የተፃፈውና የተዘጋጀው ለስሉው ፉድ ፕሬዚዲያ አምራቾችና ለሁሉም የንብ ምግብ ማህበረሰቦች ታስቦ ነው።
በአነስተኛ አናቢዎች ለአነስተኛ አናቢዎች የተፃፈ ነው።
እርስዎ መመሪያው ጠቃሚ ሆኖ እንደሚያገኙት ተስፋ እናደርጋለን። በሚቀጥሉት አመታትም በቴራ ማድሬ አውታር በኩል በሚሰበሰቡ የጥቅማ ሃሳቦች አማካኝነት መመሪያው እየተሻሻለ ተጨማሪ ጉዳዮችን የሚዳስስና ይበልጥ ጠቃሚ እንደሚሆን ተስፋ አለን።

የንቦች በረከት

ምስሎች ቅንብር
ዲዬጉ ጋኒ

ጽሑፍ
ማሲሚሊያኖ ጉቲ፣ ዲዬጉ ጋኒ

ትርጉም
አስኒወርድወርክስ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ተባባሪዎች
ውሎ ቦልዛኪኒ፣ ክሪስ ጉድበር፣ ጆን ኧርቪንግ፣ ሲሬና ሚላኖ፣ ግራዚያ ኖቬሊኒ

ሽፋን ገፅ
የንብ አመራረት ምስል በዲዬጉ ጋኒ

ግራፊክ ዲዛይንና ዝግጅት
ክላውዲያ ሳልዬቲ

ህትመት
ሃይ ፕሮፋይል ኃላ.የተ.የግ.ማ. አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የህትመቱ ዝግጅት አስተባባሪ ደጋፊ ስሎው ፉድ የብዝሃ ህይወት ፋውንዴሽን ሲሆን፣ ለዚህ ለተባበሩ ወገኖች ምስጋና ይገባል::
ዘውዲ አባዲ አለሙ - የኢትዮጵያ ማር ፕሬዚዲያ አስተባባሪ
አስፕሮምዬሌ፣ ፕዬሞንቴ የማር አምራቾች ማህበር
ሜዲካል ኮፕሬሽን ኮሚቲ (ችችም)፣ የፕሮጀክት አጋር
ኮናፒ፣ ተፈጥሮአዊ አናቢዎች እና ገበሬዎች
ራፋሌ ዴሎቲዮ፣ በኢትዮጵያ የጣሊያን አምባሳደር
የጀመርን ቴክኒካዊ ትብብር (ግትዝ) የፕሮጀክት አጋር
ጂያንሉካ ፕሬሲ፣ የኢትዮጵያ ፕሬዚዲያ ተባባሪ

እንዲሁም ድጋፍ ያበረከቱ
ኮናፒ፣ ተፈጥሮአዊ አናቢዎች ገበሬዎች
ሴንት ጉቤይን ቬትሪ

«ንብ ከምድረ ገጽ ቢጠፉ፣
የሰው ልጅ ከአራት አመት
በላይ በህይወት መቆየት
አይችልም»

አልበርት አንስታይን

SAINT-GOBAIN
VETRI

CONAPI
APICOLTORI
ED AGRICOLTORI
BIOLOGICI
coltivatori di biodiversità